# የቤተክርስቲያን አባልነት

1.የቤተክርስቲያን አባልነት አስፈላጊነት

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “መልካም እረኛ እኔ ነኝ አብም እንደሚአውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃቸዋለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል..........ድምፄንም ይሰማሉ” ዮሐ 10፤14-15 እንዳለው ካህን ወይም ቄስ መንጋቹን ካላወቀና እነርሱም እረኛቸውን /አባታቸውን/ እስካላወቁ ድረስ የእረኝነት ሥራ የለም። ለዚህም ነው ጌታችን ቅዱስ ጴጥሮስን ሦስት ጊዜ ያህል “በጎቼን ፤ ጠቦቶቼን እና ልገሎቼን አሰማራ”ያለው ። ዮሀ 21

እውነተኛ እረኛ በጎቹን በመልክም በድምፅም የሚያውቃቸውና እነርሱም የሚያውቁት ምንደኛ ያልሆነ በዋናው በር የሚገባው ነው። ዮሐ 10፤ እግዚአብሔር የራሱን መንጋ ያውቃል።

በቤተክርስቲያን ጥላ ውስጥ የሚኖሩ የቤተክርስቲያን አባላት ሁሉ የእግዚአብሔር መንጋዎች ናቸው።እኒህ አባላት ቤተክርስቲያን ይባላሉ።የምዕመናን ስብስብ (ኤክሊሲያ)ይባላል።በቤተክርስቲያን አባልነት ውስጥ በቃለ አዋዲ ሥርዓት ያልተመዘገቡ ግን  የክርስቲያን አባላትና የእግዚአብሔር ተከታዮች ለማለት በቂ ማረጋገጫ አልተሰጠም። ስለሆነም የሃይማኖት አባል፤ ሃይማኖተኛ፤ ኦርቶዶክሳዊና ክርስቲያን ለመባል በግድ የቤተክርስቲአን አባል መሆን ያስፈልጋል። መዝ 90፤ 1-16

2.ቤተክርስቲያን አባል የሚያተኩርበት

የቤተክርስቲያን አባል ሲባል ከቤተክርስቲያን አገልግት፤ ከቤተክርስቲያን አገልጋዮችና ከራሱ ምን ጥቅም እንደሚፈልግ ያገናዘበ መሆን ሲችል ነው።

አንድ ሰው ከቤተክርስቲያን ምን ጥቅም ሊያገኝ ይችላል? ለምሳሌ ያህል በደስታው ጊዜ፤ በጥልቅ ሀዘኑ ጊዜ፤በችግሩ ጊዜ፤በሰርግ ፤በሞት፤በክርስትናና በተለያዩ የግልና የማህበራዊ ጉዳዮች አንድ ክርስቲን ከቤተክርስቲያን የሚገባውን አገልግሎት ማግነት ይችላል። ይህ ሲባል ግን ቤተክርስቲያንም ከምዕመኑ የሚፈልገውን የአባልነት መንፈሳዊ ግዳጅ ያሟላ መሆን አለበት እንጂ እንዲሁ የእግዚአብሔር ቤት ስለሆነች ብቻ የነፃ አገልግሎት ለዘፈቀደው ነዋሪ ሁሉየማዳረስ ግዳጅ አልተታለባትም።

ምንም እንኳን አለአድልዎ ለሁሉም ወንጌልን እንድትሰብክና ፈውስ እንድታዳርስ ተልዕኮና አደራ የተጣለባት ቤተክርስቲያን ብትኖረንም አንድ አንዶች ከላኢ የተጠቀሱ ስጋዊ ሁኔታዎች ገጠሞች ከሌላቸው በቀር ሁሌም ከራሳቸው ሚጠበቀውን የማያሟሉ በመሆናቸው እንዲህ ያሉትን የቤተክርስቲያን አገልግሎት ሳይገባቸው አገልግሎቷን በእኩሌታ የማዳረስ ግዳጅ አልተጣለባትም።ለዚህ ሲባል ነው ቀኖና ቤተክርስቲያን የተሰራው። በቀኖና ቤተክርስቲያን ድንጋጌ ክርስቲያንና በቤተክርስቲያን ተጠቃሚ የሚሆኑ ሁሉ መስፈርት አላቸው። የአባልነት መታወቂያና የአባልነት ክፍያ የማያሟሉ ሁሉ ቤተክርስቲያን አታውቃቸውም የሚለውን ጨምሮ ሌሎች አብይ ነጥቦችን ትኩረት መድረግ ግድ ይላል።

ሌላው ከቤተክርስቲያን አባቶች የሚገኘውን ጥቅም ማወቅ ነው። አንድ ክርስቲያን የሃይማኖቱ አባል እስከሆነ ድረስ ቤቱ መጎብኘት ጠበል መረጨት/መጠመቅ/ አለበት። ለመንፈሳዊነት እስከተዘጋጀ ድረስም ከአበ ነፍሱ ንስሀ መቀበልና ለቅዱስ ቁርባን እራሱን ማብቃት ይችላል። ይህ ባልተሟላበት

ሁኔታ ከመዳን ዋና አላማ ውጭ ሆኖ የህዝብ ቁጥር ከፍ ማለት ብቻ ከቤተክርስቲያን የእረንኝነት መስመር ጋር ስለማይጣጣም ሙሉ አባል ኢያሰኝም።

3.በቤተክርስቲያንና በሕዝበ ክርስቲያን መካከል ያለው ግንኙነት

በቤተክርስቲያን ውስጥ ወጣቶች፤ ሴቶች፤ ወንዶች፤ ሰራተኞችና በተለያየ እድሜ እንዲሁም የስራና የአ እንዲሁም የስራና የአቋም ሁኔታ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ልንገናኛቸው እንችላለን። የሁሉም ስምና አድራሻ በቤተክርስቲያን ውስጥ ተመዝግቦ ሊያዝ ይችላል፡፡ ለሁሉም የሚሰጠው አገልግሎት መንፈሳዊና ተመሳሳይ ብቻ ስለሆነ ሁሉም የሚጠብቀው ከቤተክርስቲያን ሥርአት አኳያ የሚገኘውን መንፈሳዊ ጥቅም ብቻ ሊሆን ይገባል።

4. የቤተክርስቲያን አባላት ልዩ መለያ

በጥምቀት ተወልዶ ሀብተወለወድና ስመ ክርስትና የተቀበለ ሁሉ የቤተክርስቲያን አባል እንደሆነ ይታመናል። "ያመነ የተጠመቀ ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል" ተብሏልና ማር 16፤16 በእድሜና በፆታ፤በስራና በትምህርት በሌሎችም ሁኔታዎች ያለን ልዩነት የቤተክርስቲያንን አባልነትና የክርስቶስ አካል የመሆን ምልክቶች አይደሉም።

የቤተክርስቲያን ልዩ መለያዎች የሚባለው መንፈሳዊነት ብቻ ነው። የተጠመቁ አባላት፤ ንስሃ የገቡ የሚቆርቡና በተእግስታቸውና በምግባር አርአያነታቸው የሚገለጹ፤ በትጋህ በጾም በፀሎትና በማህበራዊ ተሳትፎ ንቃታቸው የሚለኩ ትሁታን እኒህ የሃይማኖት አባላት ናቸው። የስም ክርስቲያን በመሆን ቅዳሴ የማያስቀድሱትን፤ ትምህርተ ወንጌል የማይማሩትን፤ የቤተክርስቲያንን መርሃግብር የማይከታተሉትን ሁሉ ግን የቤተክርስቲያን አባል ለማለት እውነት ይቻላልን?

መንፈሳዊ የቤተክርስቲያን ኣባላት አንኳን አዋቂዎች ሕጻናቱም አርአያቸው ይሰብካል። በአለባበሳቸው፤ በአነጋገራቸው፤በተስፋቸው፤ በአመጋገባቸው በሌሎችም የዕለት ተዕለት ኑሯቸው ሁሉ እግዚአብሔርን ይገልጹታል። እንዲህ በተግባር የሚገለጽ ማንነት የያዘ ነው የቤተክርስቲያን አባል ተብሎ የሚታወቀው

ይቀየጥላል.......................